ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

ትምህርት ቤታችን ከቨርጂኒያ የወንጀል ፍትህ አገልግሎት ክፍልና ከቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር የቨርጂኒያ ትምህርት ቤት አጠቃላይ እንቅስቃሴና የስራ ሁኔታዎች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ከጃንዋሪ 2024 ጀምሮ በ 9፣ 10፣ 11 እና 12 ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች የክፍል መምህራኖችና ሰራተኞች ላይ የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳሉ፡፡ የተማሪ የዳሰሳ ጥናት አላማው የተማሪን ድጋፍ፣ የተማሪ ተሳትፎ፣ የትምህርት ቤት ስነምግባርና የደህንነት ሁኔታዎችን በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት መለካት ነው፡፡ ይህ መረጃ ደህንነቱ የተጠበቀና ደጋፊ የትምህርት ቤት አካባቢን የሚያፈሩ ትምህርታዊ ተሞክሮዎችን ለመምራት የሚጠቅም ነው፡፡

የተማሪው ዳሰሳ በ ጥር 30 - የካቲት 2 ይጠናቀቃል፡፡ ጥናቱ የልጅዎን ስም የማይጠይቅና ሁሉም መልሶች ስም አልባ ናቸው፡፡ መምህራንንና ኃላፊዎችን ጨምሮ ማንም ሰው ልጅዎ የዳሰሳ ጥናቱ እንዴት እንደመለሰ አያውቅም፡፡ የልጅዎን የዳሰሳ ጥናት መልሶች ማግኘት አይችሉም፡፡ በተማሪ የዳሰሳ ጥናት ላይ የተጠየቁትን ጥያቄዎች በዚህ ድረገጽ https://tinyurl.com/VaSchoolSurvey ላይ አስቀድመው ማየት ይችላሉ፡፡

የዳሰሳ ጥናቱ ተማሪዎች ስለ ትምህርት ቤታቸው የሚሰማቸውን ስሜት፣ ተማሪዎች እርስበርስ እንዲሁም ከመምህራኖቻቸው ጋር እንዴት እንደሚግባቡ፣ ተማሪዎች ስለትምህርት ቤት ህጎች ምን እንደሚሰማቸውና መምህራኖቻቸው እነርሱን ለመርዳት ያላቸውን ፍላጎት ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ የመሳሰሉ ጥያቄዎችን የሚጠይቅ ነው፡፡ እባክዎን ስለ ጉልበተኝነት፣ የአእምሮ ጤናና ራስን ማጥፋትን ጨምሮ ለአንዳንዶች ስሜታዊ ሊያደርጉ የሚችሉ ጥያቄዎች እንዳሉ ይወቁ፡፡ ስለነዚህ አስፈላጊ ጉዳዮች ከልጅዎ ጋር ለመወያየት ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነው፡፡ በእነዚህ ርእሶች ላይ መመሪያና ተጨማሪ ግብዓቶችን ለማግኘት እባክዎ https://tinyurl.com/MentalHealthdcjs ወይም https://tinyurl.com/VDOEstudentservices ይመልከቱ፡፡

በልጅዎ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች በዳሰሳ ጥናቱ ላይ ለመሳተፍ ብቁ ናቸው፡፡ የዳሰሳ ጥናቱ በፈቃደኝነት የሚካሄድ ሲሆን እርስዎ እና/ወይም ልጅዎ አለመሳተፍም ይችላሉ፡፡ ልጅዎ ካልተሳተፈ በእርስዎ፣ በልጅዎ ወይም በትምህርት ቤቱ ላይ ምንም አይነት እርምጃ የሚወሰድ አይሆንም፡፡ ልጅዎ እንዲሳተፍ **የማይፈልጉ** ከሆነ እባክዎን እስከ ***DATE*** ድረስ ለትምህርት ቤቱ ቢሮ በስልክ፣ በኢሜል ወይም በደብዳቤ ያሳውቁ፡፡

የቨርጂኒያ ትምህርት ቤት የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች በትምህርት አመቱ መጨረሻ አካባቢ ለትምህርት ቤቱ የሚሰጡ ይሆናል፡፡ ለትምህርት ቤትዎና ክፍልዎ የቀረቡ የዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡ https://tinyurl.com/VaSchoolSurvey፡፡ ውጤቶቹ በትምህርት ቤቱ፣ በክፍሉና በስቴቱ ጥቅም ላይ የሚውሉት ጥንካሬዎችን ለመለየትና ለልጅዎ እንዲሁም በስቴቱ ያሉ ተማሪዎች የትምህርት አካባቢን ለማሻሻልና አስፈላጊ የሆኑ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚያስችል ነው፡፡

በዚህ ጠቃሚ የቨርጂኒያ ትምህርት ቤቶች ጥናት ላይ ስላደረጉት ትብብር እናመሰግናለን፡፡

*Arlington Public Schools*